## መመሪያ ቁጥር 243/2013

### ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የሚከፈለውን ታክስ እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ

በአሁኑ ጊዜ በዓለም ገበያ ያለቀለት ቆዳ ፍላጎት በመቀነሱ ምክንያት በቆዳ ዘርፍ የሚታየው የኤክስፖርት ንግድ መዳከም ከፍተኛ የጥሬ ቆዳና ሌጦ ብክነት እንዲሁም በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ክምችት ያስከተለ በመሆኑ፣

ይህንን ችግር ለመቃለል ወደውጭ በሚላክ በጥሬና በከፊል በተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የተጣለውን የታክስ ማከፈያ መጤዎች ማሻሻል አስፈላጊ በመሆኑ፣

የገንዘብ ሚኒስቴር በውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ ታክስ ለማስከፈል በወጣው አዋጅ ቁጥር 567/2000 አንቀጽ 4 በተሰጠው ሥልጣን መሠረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

### 1. አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "ለውጭ ገበያ በሚቀርብ በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የተጣለውን ታክስ እንደገና ለማሻሻል የወጣ መመሪያ ቁጥር 243/2013" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ማሻሻያ

ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የተጣለውን ታክስ ለማሻሻል የወጣው መመሪያ ቁጥር 30/2004 እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

የመመሪያው አንቀጽ 4 ተሠርዞ በሚከተለው አዲስ አንቀጽ 4 ተተክቷል፡፡

"4. ለውጭ ገበያ በሚቀርብ ጥሬ እና በከፊል የተዘጋጀ ቆዳና ሌጦ ላይ የሚከፈለው ታክስ እንደሚከተለው ተሻሽሏል፡፡

ሀ) ጥሬ ቆዳና ሌጦ የዋጋው 150%
ለ) ዌትብሉ የበሬ ቆዳ የዋጋው 50%
ሐ) ፒክልድ የበግ ሌጦ የዋጋው 50%
መ) ዌትብሉ የፍየል ሌጦ የዋጋው 50%
ሠ) ክረስት የበሬ ቆዳ የዋጋው 0%

ረ) ክረስት የበግ ሌጦ የዋጋው 0%
ሰ) ክረስት የፍየል ሌጦ የዋጋው 0%

## 3. **<u>መመሪያው የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ መመሪያ ከግንቦት 21 ቀን 2011 ዓ.ም. ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

*አዲስ አበባ ግንቦት 16 ቀን 2011 ዓ.ም.*

*አህመድ ሺዴ*
*የገንዘብ ሚኒስትር*